| | |
|---|---|
| ዐይነት ፦ | *ዐምደኛ ፡ ጽሑፍ ፦ "አኃዛውያን ፡ ልቅሞች ። "* |
| ርእስ ፦ | *"የዋና ፡ ዋና ፡ የዓለም ፡ ቋንቋዎች ፡ ተናጋሪዎች ፡ ብዛት ፡ (ለ 2012 ፡ ዓ.ም.) ። "* |
| ደራሲ ፦ | *"ሥልጡንሕዝብና"* ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፦ | ነሐሴ ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፦ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፦ | *"ሥልጡንሕዝብና"* ፡ መዜንው ፥ ቍ.2012-005 ። |
| ማስታወሻ ፦ | |
| ማሳሰቢያ ፦ | (ስሕተቶች ፡ በተገኙ ፡ ወይ ፡ በተጠቈሙ ፡ ቍጥር ፡ ታርመው ፥ ዝርዝራቸው ፡ ዳግመኛ ፡ ይወጣል ። ) |

## አኃዛውያን ፡ ልቅሞች ።

statistical data | données statistiques | بيانات احصائية

# የዋና ፡ ዋና ፡ የዓለም ፡ ቋንቋዎች ፡ ተናጋሪዎች ፡ ብዛት ።

በዓለም ፡ ላይ ፡ ስንት ፡ ቋንቋዎች ፡ አሉ ፦ ለሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ቍርጥ ፡ ያለ ፡ መልስ ፡ ባይኖርም ፥ በግምት ፡ ካ 5 ፡ ሺሕ ፡ እስከ ፡ 6 ሺሕ ፡ ይኾናል ። ባንድ ፡ ወገን ፥ ተመሳሳይ ፡ ቋንቋዎች ፡ ተለይተው ፡ "ቋንቋ" ፡ ሊባሉ ፡ ስለሚያስቸግር ፥ በሌላው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፥ በሺሕ ፡ አለዚያም ፡ በመቶ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ተናጋሪዎች ፡ ብቻ ፡ ያሏቸው ፡ ትናንሽ ፡ ቋንቋዎችም ፡ ስላሉ ፥ ምን ፡ ያኽሉ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ መነገራቸው ፡ በውል ፡ ስለማይታወቅ ፡ ነው ።

ከዓለም ፡ ቋንቋዎች ፡ ኹሉ ፡ ይበልጡን ፡ ተናጋሪዎች ፡ ካሏቸው ፡ ውስጥ ፡ 16 ቱን ፡ ለይተን ፡ እንደሚከተለው ፡ ድርድረናቸዋል ። እነዚህ ፡ 16 ፡ ቋንቋዎች ፡ በተጨማሪም ፡ ሀገራውያን ፡ ቋንቋዎች ፡ ናቸውና ፥ **በልሳን** ፡ ወይም ፡ **በሀገራዊ ፡ ልሳን** ፡ ደረጃ ፡ ይመደባሉ ።

ያንድ ፡ ቋንቋ ፡ ተናጋሪዎች ፡ ብዛት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስልቶች ፡ ሊመጠን ፡ ይችላል ፦

- የእናት ፡ ቋንቋቸው ፡ የኾኑትን ፡ በመቍጠር ፤
- ከእናት ፡ ቋንቋቸው ፡ ጋራ ፡ በኹለተኛ ፡ ወይ ፡ በሦስተኛ ፡ ቋንቋነት ፡ የሚናገሩትን ፡ ጨምሮ ፡ በመቍጠር ፤
- የእናት ፡ ቋንቋቸው ፡ ጋራ ፥ የመግባባት ፡ ያኽል ፡ የሚናገሩትን ፡ ቋንቋ ፡ ጨምሮ ፡ በመቍጠር ።

ለጥቆ ፡ የተመለከተውን ፡ ተራ ፡ ያጠናቀርነው ፡ ኹለተኛውን ፡ ስልት ፡ ተከትለን ፡ ነው ።

የዋና ፡ ዋና ፡ የዓለም ፡ ቋንቋዎች ፡ ተናጋሪዎች ፡ ብዛት ።

| ደረጃ | ቋንቋ | የተናጋሪው ፡ ሕዘብ ፡ ብዛት ፡ (በሚልዮን) | ከዓለም ፡ ሕዝብ ፡ ብዛት ፡ አንጻር ፡ (በመቶኛ ፥ %) | ሀገራዊ ፡ ቋንቋ ፡ ወይም ፡ ልሳን ፡ የኾነባቸው ፡ ሀገሮች ፡ ብዛት ። |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ቻይንኛ | 1'250 ፡ ሚልዮን | 16.2% | 3 |
| 2 | እንግሊዝኛ | 1'200 ፡ ሚልዮን | 15.6% | 55 |
| 3 | ሂንዱስታኒ | 860 ፡ ሚልዮን | 11.1% | 3 |
| 4 | ኤስፓኝኛ | 490 ፡ ሚልዮን | 6.4% | 20 |
| 5 | ዐረብኛ | 400 ፡ ሚልዮን | 5.2% | 24 |
| 6 | ፈረንሳይኛ | 290 ፡ ሚልዮን | 3.8% | 29 |
| 7 | መስኮብኛ | 280 ፡ ሚልዮን | 3.6% | 6 |
| 8 | ፖርቱጋልኛ | 270 ፡ ሚልዮን | 3.5% | 8 |
| 9 | ማሌ | 260 ፡ ሚልዮን | 3.4% | 3 |
| 10 | ቤንጋሊ | 220 ፡ ሚልዮን | 2.9% | 1 |
| 11 | ፔንጃቢ | 150 ፡ ሚልዮን | 1.9% | 2 |
| 12 | ጃፓንኛ | 140 ፡ ሚልዮን | 1.8% | 1 |
| 13 | ሷሂሊ | 130 ፡ ሚልዮን | 1.7% | 4 |
| 14 | ፋርሲ | 110 ፡ ሚልዮን | 1.4% | 1 |
| 15 | ዐማርኛ | 105 ፡ ሚልዮን | 1.4% | 1 |
| 16 | ቱርክኛ | 100 ፡ ሚልዮን | 1.3% | 2 |


©አ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።